# በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ

# ብዙሃን መመሪያ ቁጥር 903/2014

የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን

ግንቦት 2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## *በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን መመሪያ ቁጥር 903/2014*

በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃንን በመላው ኢትዮጵያ ተደራሽ በማድረግ ሕዝብን ለማሳወቅ፣ ለማስተማርና ለማዝናናት እንዲሁም የሕዝብን መረጃ የማግኘት መብት ለማረጋገጥ ከማስቻሉ ባሻገር የንባብ ባህልን የሚያዳብር በመሆኑ፤

በየጊዜው የሚወጡ የህትመት መገናኛ ብዙሃንን በአይነትም ሆነ በቁጥር እንዲስፋፉ ማድረግ፤ የዜጎችን የሃሳብና የአመለካከት ብዝሃነት ለማስተናገድ እንዲሁም የአገራችንን የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ ለማጠናከር ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑ፤

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀፅ 26 መሰረት በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ለመሠማራት መመዝገብ እና የዕውቅና ምስክር ወረቀት ማግኘት በማስፈለጉ እና የምዝገባ ሒደቱን ግልፅ፣ ፍትሐዊ፣ አሳታፊ እና የሃሳብና የመረጃ ብዝሃነትን የሚያስፋፉ ማድረግ በማስፈለጉ፤

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 6(3) እና 6(5) መሰረት በየጊዜው የሚወጡ የህትመት መገናኛ ብዙሃንን ማስፋፋት፣ መደገፍና መከታተል በማስፈለጉ፤

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 አንቀጽ 12(7) እንዲሁም አንቀፅ 90(2) መሰረት ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ቦርድ ወጥቷል፡፡

## *ክፍል አንድ*
## *ጠቅላላ*

1. *አጭር ርዕስ*

   ይህ መመሪያ *"በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን መመሪያ ቁጥር 903/2014"* ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. *ትርጓሜ*

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

   1/ *"በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን"* ማለት አንድ ቋሚ ስያሜ በመያዝ በተወሰነ የጊዜ ክፍተት ሳይቋረጥ በተከታታይ እንዲወጣ ታቅዶ

ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚታተም፤ ለጠቅላላው ህብረተሰብ ወይም ለአንድ የተወሰነ የሕዝብ ክፍል እንዲደርስ ታስቦ የሚሰራጭ ጋዜጣን እና መፅሔትን የሚያካትት የህትመት ሥራ ነው፡፡

2/ ***"ሀገር አቀፍ ሥርጭት"*** ማለት ከአንድ ክልል በላይ ወይም በመላ ሀገሪቱ የሚሰራጭ ማለት ነው፡፡

3/ ***"ዋና አዘጋጅ"*** ማለት በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት ያለበት የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡

4/ ***"ይዘት ላይ የመወሰን ኃላፊነት"*** ማለት በዜና ወይም በፕሮግራም መረጣ ወይም አቀራረብ ላይ ውጤታማ ቁጥጥር ማድረግ ወይም ይዘትን መወሰን ማለት ነው፡፡

5/ ***"አሳታሚ"*** ማለት በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃንን የሚያሳትምና ለሥርጭት የሚያቀርብ ማንኛውም ሰው ነው፡፡

6/ **"አታሚ"** ማለት በየጊዜው የሚወጡ ህትመቶችን ለማተም በአሳታሚው የተመረጠ ወይም ከአሳታሚው ጋር የተዋዋለ ማተሚያ ቤት ነው፡፡

7/ **"አመልካች"** ማለት በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ለመሰማራት የምዝገባና የዕውቅና ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ ሞልቶ ያመለከተ ሰው ነው፡፡

8/ ***"የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል"*** ማለት በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ለመሰማራት ምዝገባ እና የዕውቅና ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻን ተቀብሎ መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች መሟላታቸውን በማጣራት የሚመዘግብና የዕውቅና ምስክር ወረቀት የሚሰጥ በባለሥልጣኑ ውስጥ የተቋቋመ መደበኛ የሥራ ክፍል ነው፡፡

9/ ***"ባለሥልጣን"*** ማለት የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ነው፡፡

10/ ***"ቦርድ"*** ማለት የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ቦርድ ነው፡፡

11/ ***"የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ"*** ማለት የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወይም ዋና ዳይሬክተሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ዋና ዳይሬክተር ነው፡፡

12/ ***"አዋጅ"*** ማለት የመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ቁጥር 1238/2013 ነው፡፡

13/ ***"ሰው"*** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

14/ ሌሎች በአዋጁ የተሰጡ ትርጉሞች ለዚህ መመሪያም ያገለግላሉ፡፡

15/ በወንድ ጾታ የተገለጸው አገላለጽ ሴትንም ያካትታል፡፡

## 3. *የተፈጻሚነት ወሰን*

ይህ መመሪያ፡-

1/ በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ላይ እንዲሁም፤

2/ ሀገር ውስጥ ለማሰራጨት ሲባል ወደ ኢትዮጵያ በሚገባና ዋነኛ አትኩሮቱ በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሆነ ማንኛውም በውጭ ሀገር የሚታተም በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የመመሪያው መርሆች

1/ የኢትዮጵያ ዜግነት ያለው ሰው በግሉ ወይም የሕግ ሰውነት ባለው አካል አማካኝነት ግልፅ በሆነ መስፈርትና ያለአድልኦ በመመዝገብ የዕውቅ ምስክር ወረቀት ለማግኘት እና በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ሥራ ለመሰማራት ያለውን መብት ማረጋገጥ፤

2/ ከአዋጁ ጋር የተጣጣመ የምዝገባና ዕውቅና ሥነ-ሥርአት በመመሪያ መዘርጋት፤

3/ በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃንን በማሳፋፋትና ተደራሽነቱን በማረጋገጥ የዜጎችን የመረጃ ተደራሽነት ማረጋገጥ፤

4/ በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን እንዲስፋፋ ማድረግ፣ መደገፍ፣ መከታተል እንዲሁም

5/ የባለሥልጣኑ እና ምዝገባ የሚያከናውኑ ሌሎች የክልል አካላትን አሠራር በግልፅ በተገደበ ሁኔታ መካሄዱንና ነፃና ገለልተኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

## 5. በየጊዜው የሚወጣ ህትመት መገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት

1/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ሰው በግሉ ወይም በድርጅቱ፣ አማካኝነት በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ባለቤት የመሆን መብት አለው፡፡

2/ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው ማንኛውም ድርጅት ወይም አካል በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ባለቤት የመሆን መብት አለው፡፡

3/ 25 በመቶ የሆነ የአክስዮን ድርሻው በውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት የተያዘና በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው የንግድ ድርጅት በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ባለቤት የመሆን መብት አለው፡፡

4/ በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው አንድ የንግድ ድርጅት በድርጅቱ ባለቤትነት ሥር የሚተዳደሩ አንድ የጋዜጣ፣ አንድ የመፅሔት፣ አንድ የቴሌቪዥን፣ አንድ የሬዲዮ እና አንድ የበየነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ማቋቋም ይችላል፡፡

5/ ማንኛውም መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም አካል በሕግ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ወይም የተቋቋመበትን ዓላማ ለማራመድ በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን የሚያሳትም ከሆነ ሕጋዊ እውቅና እንዳገኘ ተቆጥሮ በዚህ መመሪያ መሰረት የመመዝገብ ግዴታ አይኖርበትም፡፡

6/ አስቀድሞ በሕጋዊ መንገድ የተመዘገበ ድርጅት ከሚያከናውነው ስራ ተፈጥሯዊ ባህሪ አንፃር በየጊዜው የሚወጣ ህትመትን ማሳተም የሚያስፈልገው ከሆነ ሕጋዊ እውቅና እንዳገኘ ተቆጥሮ በዚህ መመሪያ መሰረት የመመዝገብ ግዴታ አይኖርበትም፡፡

## *ክፍል ሁለት*
## *በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ምዝገባና ዕውቅና ሥነ-ሥርዓት*

### 6. *በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ምዝገባ አመልካች*

1/ ሥርጭቱ በአንድ ክልል ውስጥ በሆነ በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በአዋጁና በመመሪያው የተዘረዘሩትን መረጃዎች በማሟላት ለመመዝገብና የዕውቅና ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለሚመለከተው የክልል አካል ማመልከት ይኖርበታል፡፡

2/ ሥርጭቱ አገር አቀፍ ወይም ከአንድ ክልል በላይ በሆነ በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና በአዋጁና በመመሪያው የተዘረዘሩትን መረጃዎች በማሟላት ለመመዝገብና የዕውቅና ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ማመልከት ይኖርበታል፡፡

3/ ባለሥልጣኑ በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን የምዝገባና ዕውቅና ማመልከቻና ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት በቴክኖሎጂ ታግዞ እንዲከናወን ማድረግ ይኖርበታል፡፡

### 7. *ስለምዝገባና ዕውቅና ማመልከቻ ቅፅ*

ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ጉዳዮች የያዘ የምዝገባና ዕውቅና ማመልከቻ ቅፅ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ የማመልከቻ ቅፁንም በድረ-ገፁ ተደራሽ በማድረግ ተሞልቶ እንዲቀርብ አማራጭ መንገድ ይፈጥራል፡፡

1/ የመስራቹ፣ የባለቤቱ ወይም የአመልካቹ ግለሰብ ወይም የድርጅቱ ስም፣ አገልግሎቱ የሚሰጥበት አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር እና የኢሜል አድራሻ፤

2/ የባለቤትነት ሁኔታ፤

3/ የዜግነት ሁኔታ፣ ድርጅቱ የተቋቋመበት ሀገር፤

4/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፤

5/ የንግድ ፈቃድና የንግድ ዋና ምዝገባ የምስክር ወረቀት፤

6/ የዋና አዘጋጅ ስምና አድራሻ፤

7/ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ከሆነ የአክስዮን ባለቤቶች ስም ዜግነት፣ አድራሻና ድርጅቱ የተቋቋመበት ሀገር፣ መመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ፤

8/ በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን አይነትና መጠሪያ ስም፣

9/ አመልካቹ ሌላ ጋዜጣ፣ መፅሄት፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና በየነ-መረብ መገናኛ ብዙሃን ያለው ስለመሆኑ፤

10/ በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃኑ የሚያሳትመው ይዘት አይነት፣ የሚሰራጭበት ቋንቋ፣ የሥርጭት ቀን፣ መጠን እና አካባቢ፣

## 8. *<u>ከማመልከቻ ቅፅ ጋር ተያይዘው ስለሚቀርቡ ሰነዶችና የምዝገባና ዕውቅና ምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ያለባቸው መረጃዎች</u>*

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ሰው በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ለመሠማራት የሚከተሉትን መረጃዎች በማሟላት ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይኖርበታል፡-

1/ አመልካቹ ግለሰብ ከሆነ የመስራቹ ወይም የባለቤቱ ስምና አድራሻ፣ ዜግነት፣ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ኮፒና 2 ጉርድ የፓስፖርት መጠን ባለቀለም ፎቶግራፍ፤

2/ የዋና አዘጋጅ ስምና አድራሻ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ኮፒና 2 ጉርድ የፓስፖርት መጠን ባለቀለም ፎቶግራፍ፤

3/ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ኮፒ፤

4/ የንግድ ፈቃድና የንግድ ዋና ምዝገባ የምስክር ወረቀት ኮፒ፤

5/ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ከሆነ በሠነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ አካል የተረጋገጠ የመመሥረቻ ፅሁፍ፣ መተዳደሪያ ደንብ፤ የአክስዮን ባለቤቶች ስም፣ የዜግነት ሁኔታ፣ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ኮፒና 2 ጉርድ የፓስፖርት መጠን ባለቀለም ፎቶግራፍ፤

6/ የአመልካቹ ድርጅትና የህትመቱ መጠሪያ ስም፣ አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታና አድራሻ፣ ስልክ ቁጥር እና የኢሜል አድራሻ፤ ድርጅቱ የተቋቋመበት ሀገር፣

7/ ማመልከቻው የቀረበው በወኪል ከሆነ በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ፅ/ቤት የተረጋገጠ የውክልና ሰነድ፣ መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ኮፒና 2 ጉርድ የፓስፖርት መጠን ባለቀለም ፎቶግራፍ፤

## 9. በየጊዜው የሚወጣ ህትመት መገናኛ ብዙሃን ምዝገባና ዕውቅና አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት ሂደት

በየጊዜው የሚወጣ ህትመት መገናኛ ብዙሃን የምዝገባና ዕውቅና አሰጣጥ ሂደት የሚከተለውን የሥራ ፍሰት ጠብቆ ይከናወናል፡-

1/ በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ሥራ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በማናቸውም ጊዜ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የምዝገባ ማመልከቻ ቅጽ በመሙላት እና በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8 የተዘረዘሩትን መረጃዎች በማሟላት የምዝገባና ዕውቅና ምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ለባለሥልጣኑ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ያቀርባል፤

2/ የባለሥልጣኑ የመገናኛ ብዙሃን ፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል የምዝገባ ማመልከቻ እንደቀረበለት፡-

ሀ) አመልካቹ በአዋጁና በዚህ መመሪያ የተቀመጡ መረጃዎችን ማሟላቱን በማረጋገጥ፤ መረጃዎቹ መሟላታቸው ከተረጋገጠ ምዝገባ በማከናወን የምዝገባና ዕውቅና ምስክር ወረቀቱን ወዲያውኑ ይሰጣል፡፡

ለ) በአዋጁና በመመሪያው ከተዘረዘሩት መረጃዎች ውስጥ ያልቀረቡለት መረጃዎች ካሉ ተሟልተው እንዲቀርቡ ለአመልካቹ በፅሁፍ ያሳውቃል፤ ተሟልቶ በቀረበለት ጊዜ በመመዝገብ የምዝገባና ዕውቅና ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

ሐ) አመልካቹ በአዋጁና በመመሪያው የተዘረዘሩትን መረጃዎች ካላቀረበ ወይም በየጊዜው ለሚወጣው ህትመት የሰጠው ሥም አስቀድሞ የተያዘ ከሆነ የምዝገባና ዕውቅና ማመልከቻውን ውድቅ በማድረግ ውሳኔውን ከነምክንያቱ ወዲያውኑ ለአመልካቹ በፅሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

መ) አመልካቾች በፍትሐዊነት መስተናገዳቸውን ለማረጋገጥ ተመሳሳይና በቂ መረጃ ይሰጣል፡፡

3/ የምዝገባና ዕውቅና ምስክር ወረቀት እንዲወስድ የተገለፀለት አመልካች በአገልግሎት ክፍያ ደንብ የሚተመነውን የማመልከቻና የምዝገባ ምስክር ወረቀት ክፍያ በመፈፀም የምዝገባና ዕውቅና ምስክር ወረቀት ይወስዳል፡፡

4/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፤

ሀ) ባለሥልጣኑ የምዝገባ ጥያቄ በቀረበለት በ30 ቀናት ውስጥ መሟላት ያለበት መስፈርት መሟላቱን አረጋግጦ ምዝገባውን በማከናወን የዕውቅና ምስክር ወረቀት መስጠት አለበት፡፡

ለ) ባለሥልጣኑ በ30 ቀናት ውስጥ የምዝገባና ዕውቅና ምስክር ወረቀት ካልሰጠ አመልካቹ ሕጋዊ እውቅና እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡

ሐ) አመልካቹ መስፈርቱን አሟልቶ ማመልከቻ ካቀረበበት ቀን ጀምሮ 30 ቀናት ካለፈው የምዝገባና ዕውቅና ምስክር ወረቀት እስከሚሰጠው ሳይጠብቅም ወደ ህትመትና ሥርጭት ለመግባት ይችላል፡፡

5/ አመልካቹ ከባለሥልጣኑ የተሰጠውን የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለንግድ ሚኒስቴር ወይም ለክልል ንግድ ቢሮ በማቅረብ ማስመዝገብ አለበት፡፡

## 10. *ተቀባይነት ስላላገኘ የምዝገባ ማመልከቻና የዕድሳት ጥያቄ*

1/ ባለሥልጣኑ የቀረበለትን የምዝገባ ማመልከቻ ውድቅ ሊያደርግ የሚችለው አመልካቹ፡-

ሀ) በአዋጁና በዚህ መመሪያ ሊያሟላ የሚገባውን መረጃ ካለቀረበ ወይም

ለ) በየጊዜው ለሚወጣው ህትመት የሰጠው ሥም አስቀድሞ የተያዘ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

2/ አመልካቹ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 9(2)(ሐ) እና 11(2) መሰረት ማመልከቻው በማናቸውም ምክንያት ውድቅ ከተደረገበት በማናቸውም ጊዜ ለባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ በማመልከት ምላሽ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል፤ የበላይ ኃላፊውም በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

3/ አመልካቹ የባለሥልጣኑ የበላይ ኃላፊ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ካለው በበላይ ኃላፊው ውሣኔ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል።

4/ ቦርዱም የአመልካቹ አቤቱታ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠትና የውሳኔውን ቅጂም በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ መስጠት አለበት፡፡

5/ በቦርዱ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀጥታ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡

## 11. *የምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለማሳደስ*

1/ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት መገናኛ ብዙሃን የምዝገባና ዕውቅና ምስክር ወረቀት በየአመቱ ይታደሳል፡፡

2/ ባለሥልጣኑ የእድሳት ማመልከቻ እንደቀረበለት፤ አመልካቹ በአዋጁና በመመሪያው መሰረት የዕውቅና ምስክር ወረቀት ለማግኘት ያቀረባቸው መረጃዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ የምዝገባና ዕውቅና ምስክር ወረቀቱን ወዲያውኑ ያድሳል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን አሳታሚ መብቶች</u>

12. <u>*በየጊዜው የሚወጣ ህትመት መገናኛ ብዙሃን አሳታሚ መብቶች*</u>

1/ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት መገናኛ ብዙሃን አሳታሚ፡-

ሀ) ተግባሩን በነፃነት የማከናወን፤ ነፃና የተለያዩ አመለካከቶች የሚንጸባረቁበትን ምህዳር የመፍጠር እና ለሃሳብ ልውውጥ መጎልበት አስተዋፅኦ የማድረግ መብት አለው፡፡

ለ) ኤዲቶሪያል ነፃነቱ የተጠበቀ ነው፤ በሥራውም ሆነ በአስተዳደሩ መንግሥትና የመንግሥት ተቋማትን ጨምሮ ከማንኛውም ሰው ነፃና ገለልተኛ ነው፡፡

ሐ) ከማናቸውም አካል ዜና ወይም መረጃን የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት፤ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ወይም ትችት የማቅረብና ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴዎችን፣ መሣሪያዎችን የመጠቀም መብት አለው፡፡

መ) የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የሕዝብን አስተያየት በመቅረጽ ሒደት የመሳተፍ መብት አለው፡፡

ሠ) በመገናኛ ብዙሃን ተቋሙ ነጻነት ላይ የሚከሰት ጣልቃ ገብነት፣ ተፅዕኖ፣ ጥቃትንና የደኅንነት ስጋትን ጨምሮ ሕገ መንግሥቱን በመፃረር የፕሬስ ነፃነትን የሚያደናቅፍ አሰራር ከተፈፀመበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ወይም አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡

ረ) በመረጠው ሕጋዊ መንገድ የመደራጀት መብት አለው፡፡

ሰ) በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ አንቀፅ 49 ከተመለከተው ውጪ ማንነቱ እንዳይገለጽ በመስማማት መረጃ የሰጠን ምንጭ እንዲገልፅ አይገደድም፡፡

ሸ) በዚህ መመርያ በግልፅ የተመለከቱ መስፈርቶችን በማሟላት የመመዝገብ፣ የዕውቅና ምስክር ወረቀትና እድሳት የማግኘት መብት አለው፡፡

ቀ) በውል ከመረጠውና ከተስማማው አታሚ ጋር የሕትመት ውል ፈፅሞ የማሳተም መብት አለው፡፡ አታሚውም የሚያዘጋጀው ውል የመገናኛ ብዙሃን አዋጅና የዚህን መመሪያ መንፈስና ግብ የማይጥስ መሆን ይኖርበታል፡፡

2/ ባለስልጣኑ በየጊዜው ለሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ሠጪ መብቶች ተግባራዊነት ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ይሰራል፡፡

## ክፍል አራት
## በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ግዴታዎች

### 13. *ፕሮግራም እና ማስታወቂያን በሕግ አግባብ ስለማሰራጨት*

በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ለሥርጭት የሚቀርብ ማንኛውም ይዘት ሕገ መንግስቱን፣ የመገናኛ ብዙሃን አዋጁን እና ሌሎች የአገሪቱን ሕጎች ማክበር ይኖርበታል፤

### 14. እርማት ወይም መልስ የመስጠት ግዴታ

1/ በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን በቀረበ ዘገባ መልካም ስሙና ክብሩ በሐሰት ወይም በአሉታዊ ጎኑ ተጎዳብኝ የሚል ማንኛውም ሰው ቅሬታ የፈጠረው ዘገባ ከተሰራጨበት ቀን ጀምሮ ባለው 3 ወር ጊዜ ውስጥ ዘገባው በቀረበበት በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን በተመጣጣኝና በተመሳሳይ አምድ ወይም ገፅ በግልፅ ያለ ክፍያ እርማት የመጠየቅ መብት አለው፡፡

2/ ቅሬታ የቀረበለት በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን የቅሬታ አቅራቢውን መብት ሊያከብር እና የሚያቀርበውን እርማትም፡-

ሀ) ሥርጭቱን ከህትመቱ በተጨማሪ በድረ-ገጹና በኢንተርኔት አማካይነት የሚሰራጭ ከሆነ እርማቱ ወይም ምላሹ በደረሰ በ24 ሰዓት ውስጥ፣

ለ) ዕለታዊ ጋዜጣ ከሆነ በ3 ቀናት ውስጥ፣

ሐ) ሳምንታዊ ጋዜጣ ከሆነ በ14 ቀናት ውስጥ፣ እንዲሁም

መ) ሌላ ዓይነት ህትመት ከሆነ በቀጣዩ እትም ውስጥ በተመጣጣኝና በተመሳሳይ አምድ ወይም ገፅ ያለ ክፍያ ሊያትምለት ይገባል፡፡

ሠ) እርማቱን ለማስተላለፍ ተጨማሪ ጊዜ ካስፈለገውም ለ3 ሳምንት ብቻ በማራዘም እርማቱን ማስተላለፍ ያለበት ሲሆን፤ የዘገየበትን

ምክንያትም በኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት ወይም በደብዳቤ ለቅሬታ አቅራቢው ማሳወቅ ይኖርበታል።

ረ) እርማቱ ወይም ምላሹ እንዲወጣ ከተጠየቀ በኋላ ህትመቱ ከተቋረጠ ጥያቄው የቀረበበት መገናኛ ብዙሃን ክፍያውን በመሸፈን በሌላ ተመሳሳይ መገናኛ ብዙሃን ላይ እርማቱን ወይም ምላሹን እንዲያወጣ ይደረጋል፡፡

3/ እርማት የማውጣት ወይም መልስ የመስጠት መብቱን የተነፈገ ሰው የህትመቱ አዘጋጅ ተገዶ መልሱን እንዲያወጣለት ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

## 15. *ስለዋና አዘጋጅ*

በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን በዋና አዘጋጅነት የሚሾም ሰው፡-

1/ የተሟላ የሕግ ችሎታ ሊኖረው ይገባል፡፡ የሕግ ችሎታውን ካጣ የተሟላ የሕግ ችሎታ ያለው ዋና አዘጋጅ መሾም ይኖርበታል፡፡

2/ በየጊዜው በሚወጣ የህትመት ውጤት በተሰራጨ ይዘት ላይ ሙሉ የሕግ ተጠያቂነት አለበት፡፡

3/ በየጊዜው የሚወጣ የህትመት ውጤትን ይዘት የመቆጣጠር እና ማንኛውም ነገር ያለፈቃዱ ታትሞ እንዳይወጣ እና እንዳይሰራጭ የማድረግ ሥልጣን አለው፡፡ ይህን ሥልጣን የሚገድብ ማናቸውም አሰራር ወይም ስምምነት ውድቅና ፈራሽ ነው፡፡

## 16. *በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን ላይ የሚገለፁ መረጃዎች*

1/ በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን በእያንዳንዱ ዕትም ላይ፡-

ሀ) የአሳታሚውን፣ የአታሚውን፣ የዋና አዘጋጁን ስምና አድራሻ፣ እንዲሁም

ለ) የህትመቱን ቅፅ፣ ቁጥር፣ ህትመቱ የሚወጣበትን ጊዜ እና ታትሞ የሚወጣበትን ቀን፣ ወር፣ ዓመተ ምህረት እና ዋጋ በግልፅ በሚታይ ቦታ ላይ ማስፈር አለበት፡፡

2/ በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን በእያንዳንዱ ዕትም ላይ መገለፅ የሚገባቸውን መረጃዎች በማይገልፁበት ጊዜ ባለሥልጣኑ በአዋጁ መሠረት የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት በ14 ቀናት ውስጥ ግዴታቸውን እንዲወጡና የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ እንዲያሳውቁት ሊያስገድድ ይችላል፡፡

## 17. *ያለክፍያ ስለሚሰጡ ቅጅዎች*

1/ ማንኛውም ሀገር አቀፍ ሥርጭት ያለው በየጊዜው የሚወጣ ህትመት አሳታሚ ህትመቱ ታትሞ ከወጣ ከ5 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የእያንዳንዱን እትም 2 ቅጂዎች ያለ ክፍያ ለብሔራዊ ቤተ-መዛግብትና ቤተ-መፃህፍት ኤጀንሲ መስጠት አለበት፡፡

2/ በአንድ ክልል ውስጥ ብቻ የሚሰራጭ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት አሳታሚ ህትመቱ ታትሞ ከወጣ ከ5 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የእያንዳንዱን እትም 2 ቅጂዎች ያለ ክፍያ ለክልሉ ቤተ-መዛግብት ወይም ለሚመለከተው ቢሮ መስጠት አለበት፡፡

## 18. *ለውጥን ስለማሳወቅ*

በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን በምዝገባ ወቅት ባቀረባቸው መረጃዎች ላይ ለውጥ ካደረገ ወይም አገልግሎቱን ካቋረጠ በ14 ቀናት ውስጥ ለውጡን ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 19. *ጥቆማ፣ ቅሬታና ግብረ መልስን ስለማስተናገድ*

በየጊዜው የሚወጣ ህትመት መገናኛ ብዙሃን አሳታሚ፡-

1/ ከአንባቢዎቹ የሚቀርብ ቅሬታን ተቀብሎ ማስተናገድ ይኖርበታል፡፡

2/ በአዋጁና በዚህ መመሪያ መሰረት ከባለሥልጣኑ ለሚቀርለት ግብረ መልስ ተገቢውን ማስተካከያ በማድረግ የወሰደውን ማስተካከያ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 20. *የአገልግሎት ክፍያዎችን ስለመክፈል*

በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን አሳታሚ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው ተመን መሰረት የማመልከቻ፣ የምዝገባና የዕውቅና ምስክር ወረቀት ክፍያ እና የዕድሳት አገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፡፡

# *ክፍል አምስት*
# *ስለአስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃዎች*

## 21. *አስተዳደራዊ እርምጃዎች*

በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን የመገናኛ ብዙሃን አዋጅን ከተላለፈ በመገናኛ ብዙሃን አዋጁ በተመለከተው መሠረት ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በየደረጃው ሊወስድ ይችላል፡-

1/ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

2/ እስከ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺ ብር) የሚደርስ የገንዘብ ቅጣት መጣል፤ እና

3/ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማገድ ወይም መሰረዝ፡፡

## 22. አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመውሰድ ሥልጣን

1/ የምዝገባ የምስክር ወረቀትን የማገድ እና የመሰረዝ አስተዳደራዊ እርምጃዎች የመወሰን ሥልጣን የባለሥልጣኑ ቦርድ ይሆናል፡፡

2/ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ የመስጠት እና የገንዘብ ቅጣት የመጣል አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመወሰን ሥልጣን የባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡

3/ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የሚወስድ አካል አስተዳደራዊ እርምጃ ከመውሰዱ በፊት፡-

ሀ) ለአገልግሎት ሠጪው ጥፏል የተባለውን ጉዳይ፣ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊጣልበት እንደሆነ፣ ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን እና የጊዜ ገደብ በፅሁፍ ማሳወቅና አስተያየት ለመስጠት እድል እንዲያገኝ ማድረግ አለበት፤

ለ) የአገልግሎት ሠጪውን አጠቃላይ የገንዘብ ሁኔታ፣ በጥፋቱ ምክንያት ያገኘውን የገንዘብ ጥቅም፣ ሕግና መመሪዎችን የማክበር እና ግድፈቶችን የመፈጸም የኋላ ታሪክ ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት፤ የገንዘብ ቅጣቱ ከተፈጸመው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## 23. የይግባኝ አቀራረብ

1/ ባለሥልጣኑ በወሰነው አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው በየጊዜው የሚወጣ ህትመት አሳታሚ ውሳኔው በደረሰው በ14 የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ቦርዱ አቤቱታው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

2/ ቦርዱ በሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው በየጊዜው የሚወጣ ህትመት አሳታሚ ውሳኔው በደረሰው በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን ለማቅረብ ይችላል፡፡

3/ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርዱ በተሰጠ በ30 ቀናት ውስጥ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## 24. *በፍርድ ቤት የሚወሰዱ ሕጋዊ እርምጃዎች*

በመገናኛ ብዙሃን አዋጅ ክፍል 6 መሰረት የሚከተሉት ሕጋዊ እርምጃዎች በፍርድ ቤት ሊወሰዱ ይችላሉ፡-

1/ የስም ማጥፋት ድርጊትን በተመለከተ በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሀን ላይ ለሚመለተው ፍርድ ቤት የፍትሃ ብሔር ክስ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ በፍትሐ ብሔር ሀላፊነት እስከ 300,000 ብር (ሦስት መቶ ሺህ ብር) የሚደርስ የህሊና ጉዳት ካሳ ሊወስን ይችላል፡፡

2/ በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሀን ላይ ለሚመለተው ፍርድ ቤት የወንጀል ክስ ሲቀርብ ፍርድ ቤቱ በወንጀል ሕግ መሰረት የምዝገባና ዕውቅና ምስክር ወረቀት እንዲታገድ ወይም እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል፡፡

3/ በአዋጁ አንቀፅ 85 መሰረት የፌዴራል ወይም የክልል ዓቃቤ ሕግ በብሔራዊ ደህንነት ላይ ከሥርጭት በኋላ በማስቀጣት ሊቀለበስ የማይችል ግልጽና ድርስ የሆነ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ሊሰራጭ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖረው፡-

ሀ) የህትመት ውጤቱ እንዳይሰራጭ ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

ለ) ዓቃቤ ሕግ ከነገሩ አጣዳፊነት የተነሳ ጉዳቱን ለመከላከል የፍርድ ቤት የማገጃ ትዕዛዝ በፍጥነት ማግኘት ባልቻለ ጊዜ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ውሳኔ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ሥርጭት እንዲታገድ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ሐ) ዓቃቤ ሕጉ አንድ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ከሥርጭት እንዲታገድ ውሳኔ በሰጠ በ48 ሰዓት ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማስታወቅ አለበት፡፡ እግዱ በ48 ሰዓት ለፍርድ ቤት ካልቀረበ እንደተነሳ ይቆጠራል፡፡

## 25. ስለ ይርጋ

በየጊዜው በሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን በተፈፀመ የወንጀል ድርጊት ላይ ህትመቱ ከተሠራጨበት ቀን ጀምሮ እስከ 1 አመት ባለው ጊዜ ውስጥ ክስ ካልቀረበ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

## ***ክፍል ስድስት***
## ***ልዩ ልዩ ድንጋጌ***

### 26. ***የባለሥልጣኑ ፈቃድና ምዝገባ ሥራ ክፍል ተግባርና ሃላፊነት***

1/ በየጊዜው የሚወጣ የህትመት መገናኛ ብዙሃን የምዝገባ ሥራዎች የሚከናወኑት በባለሥልጣኑ ውስጥ በተቋቋመ መደበኛ የመገናኛ ብዙሃን የፈቃድና ምዝገባ የሥራ ክፍል ነው፡፡

2/ በአዋጁ አንቀፅ 6(3)፣(4)፣(5)፣(11)፣ አንቀፅ 26 እና ሌሎች የአዋጁ ድንጋጌዎች መሰረት ባለሥልጣኑ፡-

ሀ) አመልካቾችን በመመዝገብ የዕውቅና ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

ለ) መገናኛ ብዙሃን አገልግሎት ተጠቃሚዎች በቀላሉና በቀጥታ ተደራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የመገናኛ ብዙሃኑን ስም፣ አድራሻ፤ የስልክ ቁጥር፣ የኢሜልና የድረ-ገፅ አድራሻ፣ የመገናኛ ብዙሃኑን ዋና አዘጋጅ ስም በመመዝገብና በማጠናቀር በባለሥልጣኑ ድረ-ገፅ ተደራሽ ያደርጋል፤

ሐ) በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያጸድቀው ተመን መሠረት የአገልግሎት ክፍያ እንዲሰበሰብ ያደርጋል፤

መ) በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአቅም ግንባታ ሥራዎችን ያከናውናል፤

ሠ) በየጊዜው የሚወጡ የህትመት ውጤቶች በአዋጁ መሰረት ማከናወናቸውን ይከታተላል፣ የተሰራጨው ይዘት የወንጀል ጥፋትን የሚያስከትል ከሆነ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፡፡

### 27. ***የመሸጋገሪያ ድንጋጌ***

1/ የመገናኛ ብዙሃን አዋጅና ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በሕግ መሰረት የተመዘገቡ በየጊዜው የሚወጡ ህትመቶች በድጋሚ መመዝገብ ሳያስፈልጋቸው ሥራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

2/ ሆኖም የባለቤትነት ሁኔታ ላይ ለውጥ ለማድረግ የሚፈልግ አሳታሚ በዚህ መመሪያ መሰረት ይመዘገባል፡፡

### 28. ***መመሪያውን ስለማሻሻል***

1/ የባለሥልጣኑ ቦርድ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል::

2/ ባለሥልጣኑ በረቂቅ መመሪያው ዝግጅት የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ያረጋግጣል፤ በቦርዱ ሲፀድቅም አሳትሞ ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ ያደርጋል፡፡

## 29. *መመሪያው የፀና ስለመሆኑ*

ይህ መመሪያ በባለሥልጣኑ ሥራ አመራር ቦርድ ከጸደቀበት ከግንቦት 9 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

***የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃን ባለሥልጣን ሥራ አመራር ቦርድ***